የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

# የአባት አደራ

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲና ከኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት የተሰጠ መግለጫ፤

ጀግናው የኢትዮጵያ ፋኖ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የወያኔን ገዳይ ወታደር እያዝረጠርጠው ነው፣ ፋኖ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል ኪዳን በገባው መሠረት ዱር ቤቴ ብሎ ከወጣ ቀን ጀምሮ ወያኔንና ግብረ አበሮቹን ሲመቸው በጠራራው ፀሐይ እየደፋው ሁኔታው ካላመቸው ደግሞ ሌሊት ጨለማን ተገን አድርጎ ከገዳዮች ጦር ሠፈር ተሽሎክሉኮ ዘልቆ በርካታዎችን ከተጋደሙበት እያሸለባቸው እሱ ግን ምንም ሣይጎዳ ወደ ዱር ቤቱ ሲመለስ እንደሰነበተ የቆመለት ሕዝባችን ምስክሩ ነው፤ ፋኖ ከወሬ ተግባር ይቅደም በሚለው መሪሁ መስረት ከመነሻው እወቁኝ፣እዩኝ የሚለውን መፈክር አላነሳም፣ ፋኖ ጠላትንና ቅጥረኞቹን እያደባይው ያለው በምስጢር በመንቀሳቀሱ ነው፤ በራዲዮ አወድሱኝ፤በተሌቪዥን አቅራሩልኝ የሚልም መርሃ ግብር የለውም፣ ሥራውን በተግባር የሚከታተለው ወገኑ ምስክሩ ስለሆነ ከራሱ አመመራር ሌላ አፈቀላጠ አይፈልግም፤ ይህ ደግሞ ፋኖ በጥራትና በብቃት ተንቀሳቅሶ የአባቱን አደራ አንዲወጣ ረድቶታል፥እየረዳውም ነው፣ ፋኖ በዛሬው ቀን እስዬው የሚያሰኝ ገድል ፈጽሟል፣በተለይ በሰሜን ጎንደር በአብደራፌና በአከባቢው በውያኔና በተላላኪዎቹ ላይ የወሰደው እርምጃ ለወገን የሚያኮራ ሲሆን ፋኖ ባደረሰው ከፍተኛ ጉዳት በርካታ ወያኔዎችና ተላላኪዎቹ ተጎድተው ወደ ሆስፒታል ሲጋዙ የቀሩት ቦታውን ለቅቀው እግሬ አወጭኝ ብለው ጠፍተዋል፣ ስለሞቱትም ሆነ ስለቆሰሉትም ስለሞቱት መረ ጃው እንደደረሰን የምናሳውቅ ሲሆን በጎንደር ከተማ በቀበሌ ፱ በወያኔዎች ተላላ ኪዎች ላይ የጅ ቦንብ በመወርወር የፋኖ ሌላኛው ክንፍ ጉዳት አድርሶ በሰላም

አምልጧል፣ ከዚህም ሌላ ፋኖዎች በአርማጭሆ በተለያዩ ቦታዎች በወያኔ ወታደሮችና ተልላላኪዎች  ላይ ከፍተኛ አደጋ ጥለዋል፤ ፋኖዎች በሕዝብ የታቀፉ ስለሆኑ ወያኔዎችም ሆኑ ወሬ አነፍናፊዎች ሊያገኙዋቸው እንደማይችሉ እርግጠኞች ነን፣ፋኖ የአባት አደራን ለመወጣት በቆርጥነት ይታገላል፤ በሚካሄደው ሕዝባዊ አመጽም ፋኖ ከፍተኛ  ሚና እንደሚጫወት በቆራትነት ለሕዝባችን ይገልጻል፣

ኢሕብፓ የፋኖን የየዕለት ዉሎ እየተከታተለ ያሳውቃል!!

ፋኖ የሕዝብ ለጅ ነው!!!

ኢትዮጵያ በልጆቿ ደም ተጠብቃ ለዘላለም ትኖራለች!!!

EPNP.INFO

EPNP

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY